የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፷
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 60
ADDIS ABABA- 30th July, 2004

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮ ዓ.ም
የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ … ገጽ ፪ሺ፰፻፰

**CONTENTS**

Proclamation No. 416/2004
the Diredawa Administration Charter Proclamation Page 2808

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮

## የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ

የድሬዳዋ ከተማ የሱማሌና የኦሮሚያ ክልሎች ወደየክልላቸው ይዞታ እንዲካለል በወቅቱ አንስተውት የነበረው ጥያቄ በህግ መሠረት የመጨረሻ ውሣኔ እስኪያገኝ በመንግስት በተወሰነው መሠረት ከ፲፱፻፹፭ ዓ.ም ጀምሮ ለፌደራል መንግሥት ተጠሪ ሆኖ ሲተዳደር የቆየ ከተማ በመሆኑ፤

ዘላቂ የሆነ ህጋዊ መፍትሄ እስኪያገኝ ድረስ የድሬዳዋ ከተማ ለጊዜው እራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ህጋዊ መሠረት መጣል ለከተማው መልካም አስተዳደርና ልማት መፋጠን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከተማው ለምስራቁ የሀገሪቱ ክፍል የንግድ፣ የኢንዱስትሪና ሌሎች አገልግሎቶች ለመስጠት አቅም እንዲኖረው ለማስቻል ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ፣

ድሬዳዋ የነዋሪዎቹ ሁለንተናዊ ብልጽግና የተጠበቀበት ዘመናዊና ተወዳዳሪ የሥራና የመኖሪያ፣ ቀልጣፋና አዋጭ ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት በፍትሀዊነት የሚሰጥበት ከተማ ሆኖ የሚተዳደርበትን ሁኔታ በግልጽ መደንገግ በማስፈለጉ፤

ለድሬዳዋ ነዋሪ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሥልጣን መስጠትና የከተማውን አስተዳደር አደረጃጀትና አሠራር ከዲሞክራሲ መርሆዎችና ከመልካም የአስተዳደር ሥርዓት እንዲሁም ከወቅታዊ የዕድገት የልማት አቅጣጫ ጋር በሚጣጣም መልኩ በህግ መወሰን በማስፈለጉ፤

## PROCLAMATION NO. 416/2004.

## DIREDAWA GOVERNMENT CHARTER PROCLAMATION

**WHEREAS,** the Diredawa City has been accountable to and directed by the Federal Government since 1993 as per the decision thereof until such a time that the then claims of the Somalia and Oromia Regions would be finally resolved;

**WHEREAS,** legal foundation that enables self-administration is necessary to ensure good governance and to expedite development in Diredawa city until a lasting solution is secured;

**WHEREAS,** it is necessary to create conducive conditions which capacitate the City to render trade, industry and other services for the eastern parts of the country;

**WHEREAS,** it is necessary to clearly legislate conditions that enable Diredawa to be governed as a modern and competitive work and residential city in which the entire well being of its residents is ensured, and efficient and cost-effective municipal service is equitably delivered,

**WHEREAS,** it is necessary to confer self-government power on the residents of Diredawa and to legally determine the organizational structures and operations of the city in conformity with democratic principles, good governance order and contemporary trends of growth and development;

ያንዱ ዋጋ 7.60
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ቻርተር ውስጥ፣

፩/ «ከተማ» ማለት የድሬዳዋ ከተማ ነው፤

፪/ «የከተማ አስተዳደር» ማለት የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫/ «ከንቲባ» ማለት የከተማውን አስተዳደር የሚመራ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ነው፤

፬/ «የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት» ማለት የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት፣ የመንገድ ሥራ አገልግሎት፣ የእሣትና የድንገተኛ አደጋ አገልግሎት፣ የክብር መዝገብ ሥራዎችን ጨምሮ የነዋሪዎችን የዕለት ተዕለት አገልግሎት፣ የመሬት ልማት እና አስተዳደር አገልግሎት፣ የከተማ ጽዳትና ውበት አገልግሉት እና የከተማው አስተዳደር የሚወስናቸውን ሌሎች አገልግሎቶችን ይጨምራል፤

፭/ «ቀበሌ» ማለት የከተማው ሁለተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡

፮/ «የሥራ ሁኔታ» ማለት የከተማው አስተዳደር ከሥራ ሀላፊዎቹና ከሠራተኞቹ ጋር ያለውን ጠቅላላ ግንኙነት የሚመለከት ሲሆን ይህም የሥራ ሰዓትን፣ ደመወዝን፣ ፈቃዶችን፣ ከሥራ በሚሠናበትበት ጊዜ የሚገባውን ክፍያ /ካለ/፣ የጤንነትና ደህንነትን፣ በሥራ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ስለሚከፈል ካሣ፣ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓቶችንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

### ፫. ሕጋዊ ሰውነት

የከተማው አስተዳደር ሕጋዊ ሰውነት አለው፡፡ በዚህ ቻርተር የተመለከቱት የሥልጣን አካላትና የከተማው ምክር ቤት በዚህ ቻርተር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በሕግ የሚያቋቁማቸው አካላት በተሠጣቸው አንጻራዊ ሥልጣንና ተግባር መሠረት በየበኩላቸው የከተማው አስተዳደር ወኪል በመሆን የየራሳቸው ህጋዊ ሰውነት ይኖራቸዋል፡፡

**NOW, THEREFORE,** in accordance with the provisions of Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Diredawa Administration Charter Proclamation No.416 /2004."

### 2. Definitions

Unless the context indicates otherwise, in this charter,

1/ "City" means the Diredawa City;

2/ "City administration" means the Diredawa City Administration;

3/ "Mayor" means the chief executive officer who governs the City Administration;

4/ "Municipal service" includes water and sewerage service, road construction service, fire and emergency service, civil status record operations encompassing other day to day services for residents, Land development and management, City sanitation and beautification and other services to be designated as such by the City government;

5/ "Qebele" means second administrative stratum of the City.

6/ "Conditions of Work" means the entire relations between the City Government and its officials and employees and shall include hours of work, salary, leaves, payments due to dismissal, if any, health and safety, compensation to victims of employment injury, grievance procedure and other similar matters.

### 3. Legal personality

The City Administration shall have legal personality. Organs of Power set out by this Charter and other bodies to be established by the City Council in accordance with this charter shall have their own respective legal personality as representatives of the City Administration.

**፬. ወሰን**

ከተማው እስከአሁን ያለውን የድሬዳዋ አስተዳደር የከተማና የገጠር ቀበሌዎች ያካተተ ወሰን ይኖረዋል:: ወደፊት የወሰን ለውጥ ማድረግ ሲያስፈልግ የከተማው አስተዳደር ከአጎራባች ክልሎች ጋር በሚደርስበት ስምምነት መሠረት መካለል ይችላል::

**፭. የሥራ ቋንቋ**

የከተማው አስተዳደር የሥራ ቋንቋ አማርኛ ነው::

**፮. የነዋሪዎች መብት**

፩/ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት እና በሌሎች የሀገሪቱ ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ:-

ሀ. የከተማው ነዋሪዎች በከተማው አስተዳደር የፖሊሲ፣ የአስተዳደርና የበጀት ጉዳዮች በቀጥታና በተወካዮቻቸው አማካኝነት የመምከርና የመወሰን መብት አላቸው፤

ለ. ስለከተማው የሚወሰኑ ጉዳዮችን በሚመለከት መረጃ የማግኘት፣ ሀሳብና ጥያቄ የማቅረብ እና መልስ የማግኘት መብት አላቸው፤

ሐ. ነዋሪዎች የከተማው አስተዳደር የሚሰጠውን አገልግሎት በእኩልነት፣ በግልጽነትና በፍትሀዊነት መርህ መሠረት የማግኘት መብት አላቸው፤

፪/ የከተማው አስተዳደር ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ በጀት፣ የሥራ ዕቅድና መመሪያ ለነዋሪዎች ይፋ ማድረግ አለበት::

**፯. ስለምርጫ**

በዚህ ቻርተር መሠረት በየደረጃው ለሚቋቋሙት የከተማው አስተዳደርም ምክር ቤቶች የሚካሄዱ ምርጫዎች በሀገሪቱ የምርጫ ሕግ መሠረት ይከናወናሉ::

**ክፍል ሁለት**

**የከተማው አስተዳደር ዓላማ፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር**

**፰. ዓላማ**

የከተማው አስተዳደር የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል:-

፩/ ብቁ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት መልካም የአስተዳደር ሥርዓት፣ ቀልጣፋና ፍትሐዊ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት እንዲሁም አስተማማኝ ፀጥታና ማህበራዊ ትስስር የተረጋገጠበት ከተማ የማድረግ፤

**4. Boundary**

The City shall have a boundary, which includes the existing urban and rural Qebeles. In the event of a need of making a change in its boundary in the future, the City Administration may delimit it as per agreements to be made with neighboring Regions.

**5. Official language**

The official language of the city Administration is Amharic.

**6. Rights of Residents**

1/ With out prejudice to the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and other laws of the country the residents of the City have the right;

a. to directly or through their representatives, deliberate and decide on policy, administrative and budgetary matters of the City Government;

b. to seek and receive information; forward their opinions, invoke questions, and receive replies concerning matters to be decided about the city;

c. have the right to get services to be rendered by the City Administration in accordance with the principle of equality, transparency and equity.

2/ Policies, budget, plans and directives of the City Administration must be publicized to residents.

**7. Election**

The elections of the City to be held according to this Charter shall be conducted according to the electoral law of the country.

**PART TWO**

**OBJECTIVES, ORGANIZATION, POWERS AND FUNCTIONS**

**8. Objectives**

The City Administration shall have the objective to

1/ institute good governance in which effectiveness transparency and accountability to the residents dwell as well as to make a city in which expedient and equitable municipal services and reliable security and social harmony are ensured;

፪/ አመቺ የመኖሪያና የሥራ ሁኔታ የመፍጠር፣ እንዲሁም ነዋሪዎች የከተማውን ሁለገብ እንቅስቃሴ የሚወስኑበትንና የልማቱ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤

፫/ ከተማው የሀገሪቱ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በእኩልነት የሚኖሩበትና የባሕላቸው መገለጫ የሆነ ማዕከል እንዲሆን የማድረግ፤

፬/ የነዋሪዎች ደህንነትና ምቾት የተጠበቀበት በተለይም ህፃናት፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያንና ሌሎች የተጎዱ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተለየ ድጋፍ የሚያገኙበት ከተማ የማድረግ፤

፭/ ኢንቨስትመንትና ምርምርን በማበረታታትና በማጎልበት ለከተማው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የማምጣት፤

፮/ ለአካባቢው የንግድ፣ የኢንዱስትሪና የተለያዩ አገልግሎቶች የመስጠት፤

፯/ የአካባቢ ብክለትን በመከላከል የተፈጥሮ ሚዛኑን የጠበቀ ፅዱ፣ አረንጓዴና ምቹ ከተማ የማድረግ።

## ፱. የከተማው አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር

የከተማው አስተዳደር በዚህ ቻርተር ተለይተው በተሰጡት ጉዳዮች ላይ የሕግ አውጪነትና የዳኝነት ሥልጣን እንዲሁም በፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ዝርዝር ተለይተው ባልተካተቱ ጉዳዮች ላይ የሕግ አስፈጻሚነት ሥልጣን የሚኖረው ሆኖ፡-

፩/ የከተማውን ልማት የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ አዋጆችንና ደንቦችን እንዲሁም የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት ዕቅዶችን የማውጣትና በሥራ ላይ የማዋል፤

፪/ የከተማው አስተዳደር

ሀ. ማዘጋጃቤታዊ የሆኑና ያልሆኑ አካላት የማቋቋም፤

ለ. የልማት ድርጅቶች ህጋዊ አካል አድርጎ በራሱ ወይም ከግሉ ዘርፍ ወይም ከሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ጋር አግባብ ባለው ህግ መሠረት በሽርክና የማቋቋም፤

ሐ. ቀበሌዎችን የማቋቋምና ወሰናቸውን የመወሰን እንዲሁም የበጀት ድጎማ የመመደብ፤



2/ create favorable conditions of living and work as well as to facilitate conditions in which residents determine the overall operations of the City and become beneficiary of its development;

3/ make a centre where Ethiopian nations, nationalities and peoples reside in equality and express their cultures;

4/ make a city where the well-being and comfort of residents is safe kept and particularly where children, women, persons with disabilities, elderly people and other disadvantaged segments of society avail of special support;

5/ bring about speedy economic development through the encouragement and enhancement of investment and research;

6/ render trade, industry and various services for its surrounding areas;

7/ make the City a naturally balanced, clean, green and favorable environment through the prevention of environmental pollution.

## 9. Powers and functions of the city Administration

Having powers to make laws and exercise judicial powers specifically conferred on it by this charter as well as executive powers and functions over matters that have not specifically been included in the details of the powers and functions of the Federal Government executive organs,

1/ the City Administration shall issue and implement policies, proclamations, and Regulations as well as adopt economic and social development plans concerning the development of the city;

2/ the City Administration shall:-

a) establish municipal and non-municipal bodies on the City;

b) constitute public enterprises as legal entities on its own or in partnership with enterprises of the private sector or other third parties;

c) establish Qebeles, and demarcate their borders, as well as allocate budgetary subsidy to it.

መ. የሠራተኞች እና የሀላፊዎች እንዲሁም በዚህ ቻርተር የተገለፁትን የሥልጣን አካላት ባልደረቦች የሥራ ሁኔታ የመወሰን፤

ሠ. በማዕከልና በቀበሌዎች ደረጃ የሚሰጡ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት መስጫ አማራጮችን በመጠቀምና ነዋሪውን በማሳተፍ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሀዊ አገልግሎት የማቅረብ፤ ደረጃውን የጠበቀና ተቀባይነት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት መኖሩን የማረጋገጥ፤

፫/ በከተማው ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት በህግ መሠረት የማስተዳደር፤ ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ የሆነ የግል ንብረትና የቦታ ይዞታን በሕግ መሠረት ተመጣጣኝ ካሣ በመክፈል የማስለቀቅና የመውሠድ፤

፬/ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግስት ንብረት ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፵፯/፲፱፻፷፯ መሠረት የተወረሱና የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች፣ የከተማው አስተዳደር የሠራቸውን ወይም በህጋዊ መንገድ ያገኛቸውን ቤቶች የማስተዳደር፣ የማልማት ወይም የመሸጥ፤

፭/ በዚህ ቻርተር ተለይቶ በተመለከተው መሠረት

ሀ. የከተማውን በጀት የማዘጋጀት፣ የማጽደቅና የማስተዳደር፣

ለ. በተሰጡት የገቢ ምንጮች ክልል ግብር፣ ቀረጥ እና የአገልግሎት ክፍያ በህግ መሠረት የመወሰንና የመሰብሰብ፣ ፍሬ ግብርንና የተጣሉ ቅጣቶችን በህግ አግባብ የማንሣት፣ በገቢ ማስገኛ ተግባራት የመሳተፍ እና እርዳታና ስጦታ የመቀበል፤

ሐ. ከፌዴራል መንግስት በማስፈቀድ ከሀገር ውስጥ ምንጮች የመበደርና፤

፮/ ከፌዴራል መንግስት እና ከክልል አካላትና ተቋማት፣ ከግሉ ዘርፍ፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም በፌዴራል መንግስት ፈቃድ ከልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ግንኙነቶችን የመመስረትና የትብብር ስምምነቶችን የማድረግ።

d) determine the administration and the working conditions of employees and officials of the city Government as well as the staff of other organs of power set forth by this charter.

e) identify, determine and organize municipal services to be delivered at the level of the City center and Qebele; provide efficient, effective and equitable services through the use of a variety of service delivery alternatives and the participation of the people; as well as ensure that a standardized acceptable system of service delivery is in place;

3/ administer, according to law, the land and the natural resources located within the bounds of the city; expropriate, in accordance with law, a private property and or clear and take over land possession designated as and object of public interest after having paid commensurate compensation;

4/ administer, lease, develop, sale and collect incomes from houses nationalized as per Government Ownership of Urban Lands and Extra Houses Proclamation No. 47/1975 and administered by the City Administration, and other houses which the City Administration has built or obtained in accordance with law;

5/ the City Administration shall, in accordance with the specific provisions of this Charter,

a) prepare, approve and administer the budget of the city

b) determine and collect, according to law, taxes, duties and service charges out of the sources of income specifically given to the City Administration; revoke taxes and penalties effective as per the law; participate in income-generating activities, and receive donations and gifts;

c) borrow money from domestic sources at the will of the Federal Government;

6/ the City Administration may establish relations and conclude co-operation agreements with the organs and institutions of the Federal Administration and the Regions of the country, the Private sector and nongovernmental organizations as well as, at the authorization of the Federal Government, with various international organizations;

፲. የከተማው አስተዳደር የስልጣን አካላት አደረጃጀት

፩/ የከተማው አስተዳደር በማዕከልና በቀበሌ የሥልጣን አካላት የሚከፋፈል አደረጃጀት ይኖረዋል::

፪/ የከተማው አስተዳደር የማዕከል የሥልጣን አካላት የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ. የከተማው ምክር ቤት፣

ለ. ከንቲባ፣

ሐ. የከተማው ካቢኔ፣

መ. የከተማው የዳኝነት አካላት፣ እና

ሠ. የከተማው ዋናው ኦዲተር መሥሪያቤት::

፫/ የቀበሌ አስተዳደር የሥልጣን አካላት የሚከ ተሉት ናቸው:-

ሀ. የቀበሌው ምክር ቤት፣

ለ. የቀበሌ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣

ሐ. የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ፣ እና

መ. የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች::

ክፍል ሦስት
ስለ ከተማው ምክር ቤት

፲፩. ስለ ምክር ቤት አባላት

፩/ የምክር ቤቱ አባላት በየአምስት ዓመቱ በከተማው ነዋሪ ይመረጣሉ::

፪/ የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር በምርጫ ህግ መሠረት ይወሰናል::

፫/ ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ድምጽ ወይም አስተያየት ምክንያት አይ ከሰስም፣ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም ::

፬/ ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፣ በወንጀልም አይከሰስም::

፭/ የምክር ቤቱ አባላት ነፃ ናቸው:: ተጠያቂ ነታቸውም:-

**10. Structure of The Organs of Power of The City Administration**

1/ The City Administration shall have organs of power to be organized at the level of the City center and qebele:

2/ the organ of powers of the City center shall be the following,

(a) City Council,

(b) Mayor,

(c) City Cabinet,

(d) City judicial organs, and

(e) The Office of the Chief Auditor of the City.

3/ The organs of power of qebele administration are the following:

(a) Qebele Council,

(b) Qebele chief executive,

(c) Qebele standing committee, and

(d) Qebele social Court.

## PART THREE
## The City Council

**11. Members of The City Council**

1/ Members of the Council shall be elected by the residents of the City for a term of five years.

2/ The number of member of the Council shall be determined according to the electoral law.

3/ No member of the Council may be prosecuted on account of any vote he casts or opinion he expresses in the Council, nor shall any administrative action be taken against him.

4/ No member of the Council may be arrested or prosecuted without the authorization of the Council, unless he is caught red handed for grave offences.

5/ Members of the Council are free and their accountability shall be only to:

ሀ. ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፣

ለ. ለዚህ ቻርተር፣

ሐ. ለህሊናቸው፣ እና

መ. ለከተማው ነዋሪ፣
ብቻ ይሆናል::

፮/ ማንኛውም የምክር ቤት አባል የመረጠው ነዋሪ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በሕግ መሠረት ከምክር ቤት አባልነቱ ይወገዳል::

፯/ ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል በተመረጠበት ምክር ቤት የሥራ ዘመን በፈቃዱ ካልለቀቀ ወይም ካልተሰናበተ በስተቀር በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሚከናወኑ ሌሎች ምርጫዎች ሊወዳደር አይችልም::

፰/ ማንኛውም የምክር ቤት አባል የግል ጥቅሙና የከተማው ጥቅም የሚጋጭበት ሁኔታ ሲኖር ውሣኔ ከመስጠት መገለል እና ለምክር ቤቱ ማሳወቅ ይኖርበታል:: ዝርዝሩ በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል::

## ፲፪. የከተማው ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

፩/ ለከተማው አስተዳደር የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ለማዋል የከተማው ምክር ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ አዋጅ የማውጣት ሥልጣን አለው::

ሀ. የከተማውን ማዘጋጃ ቤታዊና ማዘጋጃ ቤታዊ ያልሆኑ አካላት ለማቋቋም፣

ለ. የከተማውን አስተዳደር በጀት ለማጽደቅ፣

ሐ. የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን ለማውጣት፣

መ. በዚህ ቻርተር በተደነገገው መሠረት የከተማውን የዳኝነት አካላት ለማቋቋምና፣

ሠ. በዚህ ቻርተር መሠረት በከተማው አስተዳደር ሥልጣን ሥር በሚወድቁ የፋይናንስ ጉዳዮች ላይ ግብር እና ቀረጥ ለመጣል፣ የአገልግሎት ክፍያ ለመወሰን::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

ሀ. በሥልጣኑ ክልል ሥር በሚወድቁ ጉዳዮች ላይ ከተማ አቀፍ ፖሊሲ ያወጣል፣



(a) the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia,

(b) this Charter,

(c) their conscience, and

(d) the residents of the City.

6/ Any member of the Council may, in accordance with the law, be discharged from his membership of the Council where the electorate has lost confidence in him.

7/ No member of the Council shall be elected in other electoral polls to be conducted pending the term of office of this council according to the electoral law, unless he has resigned or he has been discharged from membership of this Council.

8/ Any Council member should restrain himself and notify thereabout where his personal interest and that of the Council are in conflict. The details thereof shall be set out by Regulations.

## 12. Powers and Functions of The City Council

1/ So as to realize the powers and function entrusted to the City Administration, the City council shall have power to promulgate Proclamations on the following matter:

(a) to establish the municipal and non-municipal organs of the city.

(b) to approve the budget of the City Administration ;

(c) to issue the structure plan of the City;

(d) to establish the judicial bodies of the City without prejudice to the provisions of this Charter;

(e) to levy taxes and duties, and set service charges, upon financial matters falling under the power of the City Administration in accordance with this charter.

2/ with prejudice the provisions of Sub-Article, The City Council shall have the following powers and functions:

(a) to adopt policies on matters falling with in the purview of its power;

ለ. በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚወጡ አዋጆች ሥልጣን ሲሰጠው ወይም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያወጣቸውን አዋጆች ለማስፈጸም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ባላወጣባቸው ጉዳዮች ላይ ደንብ ያወጣል፤

ሐ. የከተማውን የአጭርና የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ልማት ዕቅድ እና ዓመታዊ በጀት ያፀድቃል፤

መ. በዚህ ቻርተር ተለይተው በተመለከቱት የገቢ ምንጮች ላይ ግብር እና ቀረጥ ይጥላል፤ የአገልግሎት ክፍያ ይወስናል፤

ሠ. የምክር ቤቱን አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤና ፀሐፊ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ይመርጣል፤ እንዲሁም የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት ያቋቁማል፤

ረ. የከተማውን ከንቲባና ምክትል ከንቲባ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ይመርጣል፤

ሰ. በከንቲባው አቅራቢነት የከተማውን ካቢኔ አባላት ሹመት ያፀድቃል፤

ሸ. በከንቲባው አቅራቢነት የከተማውን ይግባኝ ሰሚና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶች እና ዳኞች እንዲሁም የዋናውን ኦዲተር ሹመት ያፀድቃል፤ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ያቋቁማል፤ አባላቱንም ይሰይማል፤

ቀ. በከንቲባው አቅራቢነት ተጠሪነታቸው ለም ክር ቤቱ የሆኑና አስተዳደራዊ የመዳኘት ሥልጣን የተሰጣቸው ሌሎች አካላት ፕሬዚዳንቶችንና በህግ መሠረት ሹመታቸው በምክር ቤቱ መጽደቅ ያለበትን ሌሎች ባለሥልጣናት ሹመት ያፀድቃል፤

በ. የልማት ድርጅቶችን ጨምሮ የከተማውን ማዘጋጃቤታዊ የሆኑና ያልሆኑ አካላት ያቋቁማል፤

ተ. የምክር ቤቱን ኮሚቴዎች ያቋቁማል፤ አባላቱንም ከምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ይሰይማል፤

ቸ. ምክር ቤቱ በማንኛውም ወቅት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከንቲባው ከሚያቀርባቸው ሦስት እጩዎች መካከል ምክር ቤቱ የውጭ ኦዲተር ይሠይማል፤ የውጭ ኦዲተሩ የሚያቀርበውን ሪፖርት መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል፤

(b) to issue Regulations either according to the authorization of the Proclamations of the House of Peoples' Representatives; or, in the absence of such authorization, where the Council of Ministers has not issued Regulations for the implementation of Proclamations of the House of People representatives;

(c) to approve the short-term and long-term economic and social development plans and annual budgets of the City;

(d) to levy taxes and duties on revenue areas and set service charges specifically indicated under this Charter;

(e) to elect from among its members the spokes person, the deputy spokesperson and the secretary of the Council and to establish the Secretariat of the Council;

(f) to elect, from among its members, the City mayor and the Deputy mayor;

(g) to approve the appointment of the members of the City Cabinet upon the nomination by the mayor;

(h) to approve the appointment of the president, the vice president and the judges of the City Appellate and first Instance Courts and the appointment of the chief Auditor as well as to establish the Judicial Administration Commission and to designate its members;

(i) to approve the appointment of presidents of other bodies having judicial powers and accountable to it and of other officials shoes appointments to be so approved by the City Council as per the law;

(j) to establish municipal and non-municipal bodies, including the public enterprises of the City;

(k) to establish the committees of the Council and to designate their members from among its members;

(l) designate an external auditor from among 3 candidates to be proposed by the mayor at any time and where it so requires, and to examine and render decision upon the report to be submitted by the external auditor;

ጎ. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችን የጥራት ደረጃና የአገልግሎት ክፍያ ያፀድቃል፣

ነ. የቀበሌ ምክር ቤት አባላትን ብዛት ይወስናል፤

ኘ. በሚያወጣው ቀመር መሠረት የቀበሌማዎችን የበጀት ድጎማ ይመድባል፤

አ. ከከንቲባው ወይም ተጠሪነታቸው ለምክር ቤቱ ከሆኑ አካላት የሚቀርቡለትን ወቅታዊ ሪፖርቶች መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል፤

ከ. በፌዴራል መንግስት በተፈቀደው መሠረት ከሀገር ውስጥ ምንጮች ጋር የሚደረጉ የብድር ስምምነቶችን መርምሮ ያፀድቃል፤

ኸ. ለምክር ቤቱ አባላት የሥነ ምግባር ደንብ ያወጣል፤

ወ. የከተማው ከንቲባ፣ ምክትል ከንቲባ፣ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ የከተማው ካቢኔ አባላት፣ ዋና ኦዲተር ወይም ሌሎች የምክር ቤት አባላት የሥነ ምግባር ጉድለት ፈጽመዋል በሚባልበት ጊዜ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ምርመራ ያደርጋል፤ ምስክሮች ይሰማል፤ ሌላ ማስረጃ እንዲቀርብ ያደርጋል፤ ውሣኔም ይሰጣል::

**፲፫. <u>የከተማው ምክር ቤት የሥራ ዘመን እና የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት</u>**

፩/ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል:: ምክር ቤቱ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ ይኖረዋል፤ መደበኛ ስብሰባው በየሦስት ወሩ ይሆናል::

፪/ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤ የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈጉባኤው ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት::

፫/ በማንኛውም የምክር ቤቱ ስብሰባዎች ከአባላቱ ጠቅላላ ቁጥር ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል::

፬/ በማንኛውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ውሣኔ ሊተላለፍ የሚችለው በስብሰባው ላይ የተገኙት አባላት ከግማሽ በላይ ሲደግፉት ነው::

፭/ ለከተማው ፀጥታ ወይም ደህንነት ወይም የግለሰቦችን ወይም የሕጋዊ አካላትን ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር የምክር ቤቱ ስብሰባ ለሕዝብ ክፍት ይሆናል::

(m) to approve the standard of quality of municipal services and service charges;

(n) to determine the number of the members of Qebela Councils;

(o) to allocate budgetary subsidy to Qebeles according to the formula it adopts;

(p) to examine and decide upon the reports to be submitted to it by the mayor and or by organs that are accountable to its;

(q) to approve loan agreements with domestic sources as per the authorization of the Federal Government;

(r) to issue the Code of conduct of the members of the Council;

(s) to conduct investigation according to the Regulations it issues, where it is alleged that the City's mayor, deputy mayor, the Council's spokesperson, deputy spokesperson, the City's Cabinet members, or the chief auditor as well as other members of the Council have violated the Code of conduct; hear witnesses; see to it that other evidences are produced; and render decisions.

**13. Term of Office of the City Council and Its meeting Procedures**

1/ The term of office of the council shall be five years. The council shall have regular and extraordinary meetings and the regular meeting shall be held every three month;,

2/ There shall be a quorum where more than half of its total members are present in a meeting of the Council;

3/ A decision may be passed in any meeting of the Council where more than half the members in attendance second it;

4/ The meetings of the Council shall be open to the public unless it is otherwise necessary for the protection of the city's security and safety as well as for the interest of individuals and juridical persons;

5/ The spokesperson of the Council may call an extraordinary meeting; and he shall be duty bond to call an extraordinary meeting where more than half the members of the Council so demand;

፮/ ምክር ቤቱ ስለአሠራሩ የሚወስን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል::

**፲፬. የከተማው ምክር ቤት መዝገብ አያያዝ**

ምክር ቤቱ አሠራሩን እና ውሣኔውን የሚመዘግብበት መዝገብ ይኖረዋል፤ ለከተማው ፀጥታ ወይም ደህንነት ወይም የግለሰቦችን ወይም የሌሎችን መብት ይጋፋል ተብሎ በምክር ቤቱ ካልተወሰነ በስተቀር መዝገቡ ለሕዝብ ግልጽ ይሆናል::

**፲፭. ስለምክር ቤቱ ተጠሪነትና መበተን**

፩/ የከተማው ምክር ቤት ተጠሪነት ለፌዴራሉ መንግስትና ለከተማው ነዋሪዎች ይሆናል::

፪/ የከተማው ምክር ቤት ሊበተን የሚችለው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በራሱ ውሣኔ ይሆናል::

፫/ ሕገመንግስቱን አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር በከተማው ምክር ቤት ሲፈፀም ወይም የከተማው አስተዳደር ፀጥታንና ድንገተኛ ሁኔታን መቆጣጠር ሲያቅተው

ሀ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማውን አስተዳደር ማፍረስ፣ የሽግግር አስተዳደር ማቋቋም እና የሽግግሩ ወቅት የሚቆይበትን ጊዜ መወሰን ይችላል::

ለ. የፌዴራሉ መንግስት በሥልጣን ላይ ያለውን አስተዳደር ያሰናብታል:: ለከተማው የሽግግር አስተዳደር ያደራጃል፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተወሰነው መሠረት ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል::

፬/ የከተማው ምክር ቤት በራሱ ውሣኔ

ሀ. የሥልጣን ዘመኑ ከማለቁ በፊት አዲስ ምርጫ ለማካሄድ ሊበተን ይችላል::

ለ. በጣምራ የአስፈፃሚነት ሥልጣን የያዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራነት ፈርሶ በምክር ቤቱ የነበራቸውን አብላጫነት ያጡ እንደሆነ የከተማው ካቢኔ ተበትኖ በምክር ቤቱ ባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌላ ጣምራ ካቢኔ በአንድ ሣምንት ጊዜ ውስጥ ለመመስረት እንዲቻል በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ይጋበዛሉ:: የፖለቲካ ድርጅቶች አዲስ ካቢኔ ለመፍጠር ወይም የነበረውን ጣምራነት ለመቀጠል ካልቻሉ ምክር ቤቱ ይበተናል::

6/ The Council shall issue internal Regulations that determine its operations;

**14. Records Keeping of the City Council**

The council shall have a register for its proceedings and decisions. The register shall be public unless the council decides that it endangers the security or safety of the city or that it violates public morality or the rights of others.

**15. The Accountability and Dissolution of the Council**

1/ The accountability of the City Council shall be to the Federal Government and to the Residents of the City;

2/ The dissolution of the City Council may be effected by the House of Peoples' Representatives or by its own decision. Without prejudice to Article 61(3) of this Charter;

3/ The City Council may be dissolved by the Federal Government,

a) where the City Council commits an act that endangers the constitution or where the City Council fails to Control security and emergency situation, the House of Peoples' Representatives may dissolve the City Administration, establish transitional administration and determine the duration of the transitional administration and determine the duration of the transitional period;

b/ the Prime Minister shall ensure the implementation of the decision under (a) of this Sub-Article.

4/ Where the City Council dissolves by itself,

a) the City Council may, before the lapse of its term of office, conduct a new election;

b) where a coalition of political parties seizing executive power breaks up and fails to occupy the majority seats of the Council, the Cabinet shall be dissolved, and the political parties in the council shall be invited by the Ministry of the Federal Affairs to form a coalition Cabinet within a week. If the political parties fail to form a new Cabinet or to continue the coalition, however, the City council shall be dissolved;

ሐ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ /፩/ /ሀ/ ወይም /ለ/ መሠረት ምክር ቤቱ የተበተነ እንደሆነ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አዲስ ምርጫ መደረግ አለበት::

መ. ምርጫው በተጠናቀቀ በሠላሳ ቀናት ውስጥ አዲሱ የከተማው ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል::

ሠ. የከተማው ምክር ቤት ከተበተነ በሁዋላ ከተማውን የሚመራው ሥልጣን ይዞ የነበረው የሕግ አስፈፃሚ አካል የዕለት ተዕለት የአስፈፃሚነት ሥራ ከማከናወንና ምርጫ ከማካሄድ በስተቀር አዲስ ሕጎችን ማውጣት፣ ነባር ሕጎችን መሻር ወይም ማሻሻል አይችልም::

**፲፮. የከተማው ምክር ቤት አፈ - ጉባዔ**

አፈ-ጉባኤው ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ሆኖ፣

፩/ የሥራ ዘመኑ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፤ ሆኖም ሥራውን በፈቃዱ ሲለቅ፣ ወይም በምክር ቤቱ ከሀላፊነት ሲታገድ፣ ወይም የምክር ቤት አባልነቱ ሲቋረጥ የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነቱ ሊሰናበት ይችላል፣ ዝርዝሩ በምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፤

፪/ የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ይመራል፤

፫/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ምክር ቤቱን ይወክላል፤

፬/ የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይጠራል፤ ይመራል፤ የምክር ቤቱን ኮሚቴዎች ያስተባብራል፤

፭/ የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል::

፮/ የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች በመንግስት ሠራተኛ አስተዳደር ሕግ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

፯/ ምክር ቤቱ ያፀደቃቸው ሕጎች በነጋሪት ጋዜጣ እንዲወጡ ያደርጋል፤

፰/ ምክር ቤቱ በአባላቱ ላይ የሚወስዳቸውን የሥነ ሥርዓት እርምጃዎች ያስፈጽማል::

፱/ በምክር ቤቱ ስለሚወሰኑት ውሣኔዎች ወቅታዊ መግለጫ ለነዋሪዎች ይሰጣል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፤ የምክር ቤቱ ሠነዶች ለነዋሪዎች ክፍት እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፲/ የምክር ቤቱን አባላት የአቅም ግንባታ ሥራ እቅድ ያዘጋጃል፤ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በመቀናጀት ያስፈጽማል፤

c) new election shall be held with in six months if the City Council is dissolved as indicated under (a) or (b) of this Sub-Article;

d) The new City Council shall commence work with in thirty days after the conclusion of the election.

e) The executive organ in power after the dissolution of the City Council may not make, amend, or repeal laws except executing day-to-day functions and conducting elections.

**16. The Spokesperson of the City Council**

**Being accountable to the Council, the spokesperson shall**

1/ have a term of years of the council but he may be removed from office by resignation suspension o9r termination of his membership; and the details thereof shall be set out by the internal regulations of the Council;

2/ direct the Secretariat of the Council;

3/ represent the Council in all its dealings with third parties;

4/ call and preside over the meetings of the Council and Co-ordinate the committees thereof;

5/ prepare the budget of the Secretariat of the Council and implement same upon approval.

6/ employ and administer the staff of the Secretariat of the Council in accordance with civil service law;

7/ ensure that laws adopted by the Council are published in the Addis Negarit Gazette;

8/ execute disciplinary measures decided by the Council on its members;

9/ give periodical briefings to the residents and notify concerned organs about decisions passed by the City Council. He shall also ensure that the documents of the Council are available and accessible to residents;

10/ prepare plan for capacity building of the members of the Council and implement it jointly with concerned executive bodies;

፲፩/ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሃገር አቻ ምክር ቤቶች ጋር የወዳጅነት ግንኙነትና የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፤

፲፪/ ከምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፲፯. <u>የከተማው ምክር ቤት ምክትል አፈ - ጉባዔ</u>

፩/ ምክትል አፈ-ጉባዔው ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔ ሆኖ

ሀ. አፈ-ጉባዔው በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሠራል፤

ለ. በአፈ-ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባ ራት ያከናውናል።

፪/ በአንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ለምክትል አፈ-ጉባዔውም ተፈጻሚ ይሆናል።

፲፰. <u>የከተማው ምክር ቤት ፀሐፊ</u>

የምክር ቤቱ ፀሐፊ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔ ሆኖ፣

፩/ ከአፈ-ጉባዔው ጋር በመመካከር የምክር ቤቱን አጀንዳ ያዘጋጃል፤ የምክር ቤቱን ቃለ-ጉባዔ ይይዛል፤ ያትማል፤

፪/ የምክር ቤቱ ኮሚቴዎች ቃለ-ጉባዔዎችና ሠነዶች እንዲጠበቁ ያደርጋል፤ በምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ቃለ-ጉባዔዎች ያሠራጫል፤

፫/ የሥራ ዘመኑ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፤ ሆኖም ሥራውን በራሱ ፈቃድ ሲለቅ፣ በምክር ቤቱ ከሀላፊነቱ ሲታገድ፣ ወይም የምክር ቤት አባልነቱን ሲያቋርጥ የሥራ ዘመኑ ሣያልቅ ከሀላፊነቱ ሊሠናበት ይችላል፤

፬/ በአፈ-ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

<u>ክፍል አራት</u>
<u>የከተማው አስፈፃሚ አካላት</u>

፲፱. <u>የከተማውን የሕግ አስፈፃሚ አካል ስለማደራጀት</u>

በምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ያለው የፖለቲካ ድርጅት ወይም አብላጫ መቀመጫ ያለው የፖለቲካ ድርጅት ከሌለ የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራ የከተማውን የሕግ አስፈጻሚ አካል ያደራጃል፤ ይመራል።



11/ create cordial relations and exchange experiences with internal and external counterpart Councils;

12/ perform other functions assigned to him by the Council.

**17. The Deputy Spokesperson of the City Council**

1/ Being accountable to the spokesperson of the Council,

a/ he shall act on behalf of the spokesperson in the absence or incapacity of the latter;

b/ he shall perform other functions assigned to him by the spokesperson;

2/ The provisions set for the under Article 16 (1) shall be applicable to the deputy spokesperson;

**18. The Secretary of the City Council**

Being accountable to the spokes person of the Council, the Secretary of the Council;

1/ shall prepare the agenda of the Council in consultation with the spokesperson, and record, publish and keep the minutes of the Council;

2/ shall ensure that the minutes and documents of the committees of the Council are recorded and kept. He shall also distribute minutes in accordance with the internal Regulations of the Council;

3/ may be removed from office by resignation, suspension or termination of his membership of the Council. The details thereof shall be set out by the internal regulations of the Council;

4/ shall perform other functions assigned to him by the spokesperson.

**<u>PART FOUR</u>**
**<u>EXECUTIVE BODIES OF THE CITY</u>**

**19. Constitution of the Executive Organ of the City**

The political party occupying the majority seats of the Council or, where such does not exist, the coalition of political parties shall constitute the executive organ of the city;

## ፳. ከንቲባ

፩/ ከንቲባው ተጠሪነቱ ለከተማው ምክር ቤትና ለፌደራል መንግስት ሆኖ የከቲማው አስተዳደር ማዘጋጃቤታዊ የሆኑና ያልሆኑ ሥራዎች አመራር ዋና ሥራ አስፈፃሚና ተጠያቂ ነው::

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ከንቲባው

ሀ. በከተማው ምክር ቤት የሚወሰኑትን ውሣኔዎች፣ የሚፀድቁትን ሕጎች፣ ዓመታዊ እቅድና በጀት ያስፈጽማል፤

ለ. የከተማው ልዩ ልዩ ፖሊሲ፣ የኢኮኖሚና የማ በራዊ ልማት እቅድ እና ዓመታዊ በጀት በካ ቢኔው ከተመከረበት በኋላ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል

ሐ. የከተማው አምባሳደር በመሆን ከተማውን ይወክላል፣ ከእህት ከተሞች ጋር የሚደረጉ ስምምነቶችን ይፈርማል፤

መ. በከተማው ውስጥ ሕግና ሥርዓትን ያስከብራል፤

ሠ. የከተማው ምክር ቤት አባላት ከሆኑና ካልሆኑ መካከል የካቢኔ አባላትን መርጦ ሹመታቸውን በከተማው ምክር ቤት ያስፀድቃል፤ ካቢኔውን ይመራል፤

ረ. የከተማው ምክር ቤት እንደአስፈላጊነቱ የውጭ ኦዲተር ለመሰየም ሲወስን ሦስት ዕጩ ኦዲተሮች ያቀርባል፤

ሰ. ካቢኔውን በማማከርና ሙያዊ ብቃትን መሠረት በማድረግ የከተማውን ሥራ አስኪያጅ በተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ይቀጥራል፤ ያሰናብታል፤

ሸ. የነዋሪዎችን ቅሬታ ያስተናግዳል፤

ቀ. በብሄራዊና በህዝብ በዓላት ሥነ-ሥርዓቶች ከተማውን ይወክላል፤

በ. የከተማው ዕቅድ፣ በጀት፣ እንዲሁም የሥራ አፈጻጸም ለሕዝብ የሚቀርብበት እና አስተ ያየት የሚሰጥበት መድረክ እንዲዘጋጅ ያደር ጋል፤

ተ. ዓመታዊ እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክር ቤቱ በሚወስነው መሰረት ወቅታዊ ሪፖርት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ እንዲሁም በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፷፩ ንዑስ አንቀጽ /፮/ በተደነገገው መሠረት ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሪፖርት ያቀርባል፤

## 20. The Mayor

1/ Being accountable to the City Council and the Federal Government, the Mayor is the chief executive officer of the city and is responsible for the management of the city's municipal and non-municipal undertakings

2/ Without prejudice to the generality of the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Mayor shall;

a) execute decisions, laws, annual plans and budgets adopted by the City Council;

b) propose to the City Council various policies, economic and social development plans, and annual budget after consultation thereon by the Cabinet and ensure the implementation thereof upon approval;

c) represent the City as an ambassador thereof and sign agreements made with Sister-City;

d) ensure the observance of law and order in the city;

e) recruit and seek the Council's approval of the appointment of Cabinet members;

f) propose three external auditors to the City Council where the latter resolves, as may be necessary, to appoint an external auditor;

g) hire the City manager by a contract of employment for a definite period of time on the basis of his professional competence and in consultation with the Cabinet;

h) hear pressing problems of residents and their grievances;

i) represent the City in national ceremonies and public holidays;

j) ensure, in consultation with concerned bodies, the preparation of public forums where plans, budget and work performances are presented for and commented by the public;

k) submit annual report to the Council., He shall also submit to Council periodical report as necessary as may be determined by the latter. Likewise he shall submit report to the Ministry of Federal Affairs according to the provisions of Article 61 (6) of this Charter;

ቸ. ደረጃውን የጠበቀ ፍትሃዊ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣

ኀ. ለከተማው የሚያስፈልገውን የድጋፍ መጠን በማዘጋጀት በከተማው ካቢኔ ከተመከረበት በኋላ ለፌደራል መንግስት ያቀርባል፣

ነ. የአዋጅ እና የደንብ ረቂቆችን በማዘጋጀት በከተማው ካቢኔ ከተመከረበት በኋላ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

ኘ. ሹመታቸው በምክር ቤቱ መጽደቅ ያለበትን ሳይጨምር የከተማውን አስፈ ጻሚ አካላት የበላይ ሀላፊዎች ይሾማል፣ የከተማው የልማት ድርጅቶችና ሌሎች አካላት የቦርድ ሰብሳቢዎችንና አባላትን ይሰይማል፣

አ. የራሱን ጽሕፈት ቤት ያደረጃል፣

ከ. በሕግ መሠረት ሽልማቶችን ይሰጣል፣

ኸ. በከተማው ምክር ቤት እና በፌዴራል መንግስት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

፫/ የከንቲባው የሥራ ዘመን የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፣ ሆኖም በራሱ ፈቃድ ሲለቅ፣ በምክር ቤቱ ከሀላፊነት ሲታገድ፣ ወይም የምክር ቤት አባልነቱን ሲያቋርጥ የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ ከሀላፊነት ሊሰናበት ይችላል:: ዝርዝሩ በምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል::

## ፳፩. ምክትል ከንቲባ

፩/ ምክትል ከንቲባው ተጠሪነቱ ለከንቲባው ሆኖ:-

ሀ. ከንቲባው በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከ ናወን በማይችልበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሠራል፣

ለ. በከንቲባው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳/፫/ የተጠቀሰው ለምክትል ከንቲባውም ተፈፃሚ ይሆናል::

## ፳፪. የከተማው ካቢኔ

፩/ የከተማው ካቢኔ ተጠሪነቱ ለከንቲባው እና በጋራ ለሚወሰነው ውሣኔም ለከተማው ምክር ቤት ሆኖ

ሀ. በፌደራል መንግስትና በከተማው ምክር ቤት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦች፣ ውሣኔ ዎችና ደረጃዎች መፈፀማቸውን ያረጋ ግጣል፣

ለ. ምክር ቤቱ ያወጣቸው ፖሊሲዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣



l) ensure that a standardized and equitable service delivery alternative is implemented;

m) prepare and propose to the Federal Government the amount of support needed from the latter after consultation thereon by the City Cabinet;

n) prepare and propose drafts of proclamations and Regulations to the Council after consultation thereon by the Cabinet;

o) appoint the heads of the executive bodies of the City other than those whose appointments must be approved b y the Council. He shall also designate the presiding chairpersons and members of the Boards of public enterprises and other bodies of the City;

p) organize his Office;

q) award prizes in accordance with law'

r) perform other functions assigned to him by the City Council and by the Federal Government;

3/ The term of years of the Mayor shall be the term of office of the Council, but he may be removed from office by resignation, suspension or termination of his membership of the Council. The details thereof shall be set out by the internal regulations of the Council.

## 21. The Deputy Mayor

1/ **Being accountable to the mayor,**

a/ he shall act on behalf of the mayor in the absence or incapacity of the latter;

b/ he shall perform other functions as assigned to him by the mayor;

2/ The provisions of Article 20 (3) shall be applicable to the deputy mayor.

## 22. The City Cabinet

1/ Being accountable to the Mayor and for its joint decision to the City Council, the City Cabinet shall;

a) ensure that proclamations, Regulations, resolutions and standards adopted by the City council and by the Federal Government are implemented;

b) ensure that policies adopted by the council are implemented;

ሐ. ከተማ አቀፍ ፖሊሲ፣ የአዋጅና የደንብ ረቂቅ ያመነጫል፤

መ. በከተማው ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ላይ ይመክራል፤ የውሣኔ ሐሳቡን ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ሠ. የከተማውን አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ይወስናል፤

ረ. በምክር ቤቱ በሚወጡ አዋጆች በሚሰ ጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦችን ያወጣል፤

ሰ. በከንቲባውና በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

፪/ የካቢኔው የሥራ ዘመን የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል::

፳፫. የከተማ ሥራ አስኪያጅ

፩/ የከተማው ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለከን ቲባው ሆኖ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አስፈ ፃሚ ነው::

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው ሥራ አስኪያጅ፣

ሀ. ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንዲቋቋም ወይም ሌሎች የአገልግሎት መስጫ አማራጮች በሥራ ላይ እንዲውሉ ለከንቲባው ሃሳብ ያቀርባል፤

ለ. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ሀላፊዎች እንዲሾሙ ለከንቲባው ያቀርባል፣ ሹመታቸው ሲፀድቅም ሥራቸውን በሕግ መሠረት ይመራል፣ ያሰናብታል፤

ሐ. ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በቀበሌ ሥራ አስኪያጅነት በተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣ ከቀበሌ ሥራ አስኪያጆች ዓመታዊና አስፈላጊ ሲሆን ወቅታዊ ሪፖርቶችን ይቀበላል፤ መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል፣

መ. ከተማ አቀፍ እና ቀበሌ ዘለል የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን በተመለከተ እቅድና በጀት ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

c) initiate citywide policies and drafts of proclamations and regulations;

d) deliberate over the annual plans and budgets of the City and forward to the City Council its recommendations thereon as well as insure the implementation thereof up on approval;

e) decide on the organizational structure of the executive bodies of the City government;

f) issue Regulations according to the authority given to it by proclamations the council makes;

g) perform other functions assigned to it by the Mayor and by the Council

2/ The term of years of the Cabinet shall be the term of office of the council.

23. **The City Manager**

1/ Being accountable to the mayor, the City manager is the executive of municipal services;

2/ Without prejudice to the generality of the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the City manager shall;

a) propose to the mayor to establish municipal bodies accountable to the City manager and to implement other service delivery alternatives,

b) propose the appointment of the heads of municipal bodies. Upon the approval of their appointments, he shall supervise their operations and discharge them in accordance with law;

c) hire, administer, and discharge competent professionals as qebele managers by contract of employment for a definite period of time. He shall also receive, examine and decide upon annual reports and, where necessary, periodical reports from Sub-City managers,

d) prepare and submit to the mayor action plans and budget proposals concerning citywide and inter-qebele municipal services and implement them upon the endorsement thereof,

ሠ. የአገልግሎት አቅርቦት መለኪያዎች እና መመሪያዎች በማጠናቀር ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ረ. ሥሉጥ፣ ውጤታማና ፍትሀዊ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት መሠጠቱን ያረጋግጣል፤

ሰ. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከቱ ውሣኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሸ. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከት የፖሊሲ ሃሳብ እና የሕግ ረቂቅ በማመንጨት ለከንቲባው ያቀርባል፤

ቀ. የከተማው ምክትል ሥራ አስኪያጅ እንዲቀጠር ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ይቀጥራል፤

በ. የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለከንቲባው ያቀርባል፤ እንደአስፈላጊነቱ ሲጠየቅም ለከተማው ምክር ቤት ወይም ለከተማው ካቢኔ ሪፖርት ያቀርባል፤

ተ. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን በተመለከተ የነዋሪዎችን አቤቱታ ያስተናግዳል፤ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በተቻለ ፍጥነት መልስ ይሰጣል፤

ቸ. በሥሩ ከሚሠሩ አካላት ሀላፊዎች የተውጣጣ የሥራ አመራር ኮሚቴ ያቋቁማል፤ ይመራል፤

ኀ. በከንቲባው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

፫/ የከተማው ሥራ አስኪያጅ በከተማው ምክር ቤት ስብሰባዎች ያለድምጽ መሳተፍ ይችላል::

**፳፬. ምክትል የከተማ ሥራ አስኪያጅ**

ምክትል የከተማው ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ሆኖ፣

፩/ የከተማው ሥራ አስኪያጅ በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሰራል፤

፪/ በከተማው ሥራ አስኪያጅ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

e) develop and propose to the mayor service delivery measurements and guidelines and implement them upon the endorsement thereof,

f) ensure the delivery of efficient, effective and equitable municipal services,

g) implement decisions concerning municipal services

h) prepare and propose to the mayo9r policy initiatives and legal drafts concerning municipal services,

i) recommend to the mayor the employment of the deputy City manager and hire him upon the approval thereof.

j) submit to the mayor or, where he is required as may be necessary, to the City Cabinet or to the City Council work performance reports.

(k) receive and hear as well as give replies as quickly as possible to the pleas of residents concerning municipal sevices.

(l) constitute and direct a management committee consitsting of underheads of municipal services.

(m) perform other functin assigned to him by the mayor.

3/ The City manager may participate without a vote in the meetings of the City Council.

**24. The Deputy City Manager**

Being accountable to the City manager, the deputy City manager shall

1) Act on behalf of the City manager in the absence or incapacity of the latter

2) perform other functions assigned to him by the City Manager.

## ክፍል አምስት
## ሌሎች አስፈፃሚ አካላት

**፳፭. የከተማው አስተዳደር ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት**

፩/ የከተማውን አስተዳደር የሥልጠት፣ የክንዋኔ ብቃት፣ የሀብት አጠቃቀምና አስተዳደር በመቆጣጠር ለከተማው ምክር ቤት ሪፖርት የሚያቀርብ የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ይኖረዋል::

፪/ የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ሥራውን የሚያከናውነው በነፃነት ነው::

፫/ ዋናው ኦዲተር ቀጥሎ ካሉት ምክንያቶች ውጭ ያለፈቃዱ የጡረታ ዕድሜ ከመድረሱ በፊት ከሥራው አይነሳም፤

ሀ. በዲሲፒሊን ጥፋት ወይም በከባድ የችሎታ ማጣት ወይም ቅልጥፍና ማጣት፣

ለ. በሕመም ምክንያት ሀላፊነቱን ለመወጣት የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ወይም

ሐ. የከተማው አስተዳደር ምክር ቤት ከሥራው እንዲነሳ ሲወስን::

፬/ የከተማው አስተዳደር ዋና ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱን በጀት በማዘጋጀት ለከተማው ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም በጀቱን ያስተዳድራል::

**፳፮. የድሬደዋ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን**

፩/ በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚቋቋም ሆኖ፣ የድሬደዋ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን፣

ሀ. ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ተጠሪ ነው፤

ለ. በዚህ ቻርተርና በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ በሚወሰነው መሠረት በውክልና ለከተማው አስተዳደር ተጠሪ ይሆናል፤ ስለሆነም የከተማውን ፖሊስ ኮሚሽን የዕለት ተዕለት ሥራዎች የመከታተል ሀላፊነት የከንቲባው ይሆናል፤

ሐ. ዕቅድና በጀቱን በማዘጋጀት ለከንቲባውና ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ያቀርባል፤ በከተማው ምክር ቤት ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤



## PART FIVE
## OTHER EXECUTIVE BODIES

**25. The Office of the City Chief Auditor**

1) There shall exist the Office of the chief auditor, which inspects and reports to the City Council the efficiency, performance effectiveness, resource utilization and administration of the City Government.

2) The office of the Chief auditor shall perform its functions independently.

3) The chief auditor shall not be removed from his office before he retires, except for his resignation or for resignation or for reasons set forth below:

a. disciplinary fault, grave incompe tence- or poor performance;

b. proven inability to fulfil his responsib- ilities because of illness; or

c. where the City Council decudes by majority vote to theat effect.

4) The chief auditor shall preoare and submit to the City Council the budget of his office and acminister it upon the approval thereof.

**26. The Dire dawa Administration Police Commission**

1) The Dire dawa City Police Commission shall be established by Regulations the Council of Ministers issue in accordance with the Federal Police Commission Establishment Proclama- tion.The Dire dawa Police Commission shall,

(a) be accountable to he Federal Police Commission;

(b) be accountable to the City Administration by delegation conferred through this Charter and the Regulations of Council of Ministers; the Mayor shall be responsible for the daily follow up of the oprations of the City Police Commission;

(c) prepare and submit its plan and budget proposal to the Mayor and to the Federal Police Commission, and implement same upon approval by the City Council.

መ. ዓመታዊና ወቅታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶቹን ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሪፖርቶቹም በከተማው ካቢኔና በከተማው ምክር ቤት ተመርምረው ውሣኔ ይሠጥባቸዋል::

፪/ የከተማው ፖሊስ ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነር በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ይሾማሉ::

፳፯. የከተማው አስተዳደር ዐቃቤ ሕግ ሥልጣን

የከተማው አስተዳደር ዐቃቤ ሕግ ሥልጣን አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በከተማው ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ ክስ ይመሠርታል፣ ይከራከራል፣ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

፳፰. የከተማው አስተዳደር የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን

የከተማው አስተዳደር በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ መሠረት የሚቋቋምና የሚሠራ የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ይኖረዋል::

ክፍል ስድስት
ስለ ቀበሌ አስተዳደር

፳፱. ስለ ቀበሌ ወሰን

፩/ በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፬ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌዎች ወሰን በከተማው ምክር ቤት ይወሰናል::

፪/ የከተማው ምክር ቤት የነዋሪዎችን አስተያየት፣ አመቺ የአገልግሎት አቅርቦት፣ የከተማ ልማት ዕቅድና የሕዝብን ብዛት መሠረት በማድረግ አዲስ ቀበሌ ሊያቋቁም ወይም ያለውን ቀበሌ እንደገና ሊያዋቅር ይችላል::

፴. የቀበሌ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር

፩/ የቀበሌ አስተዳደር ለቀበሌው ነዋሪና ለከተማው አስተዳደር ተጠሪ ይሆናል::

፪/ የቀበሌ አስተዳደር በከተማው ምክር ቤት ተለይቶ በህግ የሚወሰን ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል::

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የቀበሌ አስተዳደር:-

d) submit annual and periodical performance reports to the mayor, and the reports shall be examined and decided by the City Cabinet and the City Council.

2) The City Police Commissioner and deputy Commissioner shall be appointed by the Minister of Federal Affairs.

**27. The Diredawa Public Prosecution Office**

The Public Prosecttion Office shall prososecute shuc penal offences that fall under the jurisdication of the City Courts and darry out other relevant functions in accordance with the appropriate law.

**28. Ethics and Anti-corruption commission**

The City Administration shall have Ethics and Anti-corruption Commission which is to be established and to function in accordance with law theCity Council makes.

**PART SIX**
**QEBELE ADMINISTRATION**

**29. Boundaries of Qebekes**

1) Without prejudice to the provisions of Article 4 of the Charter, the boundaries of Qebles shall be delimited by the City Council.

2) The City Council may either establish new Qebele, or reorganize existing Qebeles taking in to account the opinions of respective residents, the suitability of service delivery, the urban development plan at stake,and the size of the population.

**30. Powers and functions of Qebele Administration**

1) Qebele Administration shall be accountable to the residents of the respective Qebele and the City Administration.

2) The power and functions of the Qebele Administration shall be determined by the law that the City Council specifically issues.

3) Without prejudice to the provisions of Sub-Article (2) f this Article, a Qebele administration shall

ሀ/ ነዋሪው በተቻለ መጠን አገልግሎት በአቅራቢያው የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

ለ/ ቀበሌውን የጥቃቅንና የአነስተኛ ንግድ ሥራ ተቋማት፣ የአካባቢ ልማት፣ የመሠረታዊና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት፣ እንዲሁም የመሠረታዊ ጤና አጠባበቅ ማዕከል አድርጎ ይሠራል፣ እንዲሁም የቀበሌውን ህግና ስርዓት ያስከብራል፣

፬/ የቀበሌ አስተዳደር የቀበሌ ምክር ቤት፣ አፈ-ጉባዔ፣ ፀሐፊ፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ቋሚ ኮሚቴ፣ ሥራ አስኪያጅ ፣ ማኅበራዊ ፍርድ ቤትና የተለያዩ አስፈፃሚ አካላት ይኖሩታል፣ ሥልጣንና ተግባራቸው በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል።

## ክፍል ሰባት
## የከተማው ፍርድ ቤቶችና የመዳኘት ሥልጣን የተሠጣቸው ሌሎች አካላት

### ፴፩. ፍርድ ቤቶች

የከተማው አስተዳደር የሚከተሉት ፍርድ ቤቶች ይኖሩታል፣

፩/ የድሬዳዋ ከተማ ፍርድ ቤቶች፣ እና

፪/ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች።

### ፴፪. የመዳኘት ሥልጣን ስለተሰጣቸው ሌሎች አካላት

የከተማው አስተዳደር የመዳኘት ሥልጣን የተሰጣቸው የሚከተሉተት አካላት ይኖሩታል፣

፩. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ፣

፪. የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት፣ እና

፫. የግብር ይግባኝ ሰሚ እና የከተማ ቦታ ማስለቀቅ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ።

### ፴፫. የድሬዳዋ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን

የድሬዳዋ ከተማ ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፣

፩/ የፍትሐብሔር ዳኝነት ሥልጣን

ሀ/ የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አፈጻጸም የሚመለከት የይዞታ ባለመብትነት፣ የፈቃድ አሰጣጥ ወይም የቦታ አጠቃቀምን በተመለከተ የሚነሱ ክሶች፣

ለ/ ከከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ እና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት የመቆጣጠር ሥልጣንና ተግባር ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክሶች፣

a/ create conditions in which the residents of the Qebele avail of services in their vicinity as close as possible.

b/ Work by using the Qebele as a center of micro-and –small business enterprises, Local development, basic and primary education, and primary health care service. It shall also insure that law and order is respected in the Qebele.

4) A Qebele shall have a Council, with its spokesperson and secretary, a chief executive, a standing committee, a manager, a social court and other municipal and non municipal bodies. their powers and functions shall be determined by law the City Council makes.

## PART SEVEN
## THE CITY COURTS AND OTHER BODIES WITH JUDICIAL POWERS

### 31. Courts

The City Government shall have the following Courts:

1) The Diredawa City Courts; and

2) Qebele Social Courts.

### 32. Other Bodies with Judicaial Powers

The City Government shall have the following bodies entrusted with; judicial powers:

1) Labour Relations Board,

2) Civil Servants Court and

3) Tax Appeals and Urabn land Clearance Appeals Commission.

### 33. Jurisdiction of the Diredawa City Courts

The Diredawa City Courts shall have jurisdiction over the following cases:

1/ Civil Jurisdiction

(a) cases of possessory right, issuance oar land use relation to the enforcement of the City Master Plan;

(b) cases arising in connection with the regulation with the regulatory powers and functions of the executive bodies of the City Government;

ሐ/ በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፶፪ በተመለከቱ የፋይናንስ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ክሶች፣

መ/ የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ እና የማዘጋጅ ቤት አገልግሎት አካላት ወይም በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ሥር ያሉ ተቋማት የሚገቧቸውን አስተዳደራዊ ውሎች በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች፣

ሠ/ በከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ እና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ወይም በከተማው አስተዳደር ሌሎች ተቋማት መካከል የሚነሱ ክሶች፣

ረ/ የከተማው አስተዳደር የሚያስተዳድራቸው ሆኖ ለንግድ፣ ለመኖሪያ ወይም ሌላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ካሉ የመንግሥት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክሶች፣

ሰ/ የስም ለውጥ አቤቱታ፣

ሸ/ የወራሽነት፣ የሞግዚትነት፣ የሚስትነት ወይም የባልነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ፣ እና

ቀ/ የመጥፋት ወይም የሞት ግምት ማስታወቂያ አቤቱታ::

፪/ የወንጀል እና የደንብ መተላለፍ ዳኝነት ሥልጣን

ሀ/ በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፶፪ ከተመለከቱት የፋይናንስ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚነሱ የወንጀል ክሶች፣

ለ/ የትራፊክና ሌሎች የደንብ መተላለፍ ክሶች፣

ሐ/ በፌዴራል ወንጀሎች ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የጊዜ ቀጠሮ፣ የመያዣና የብርበራ ትዕዛዝ እንዲሁም የዋስትና አቤቱታዎች፣ እና

መ/ ሌሎች የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በከተማው አስተዳደር ማዘጋጃ ቤታዊና ማዘጋጃ ቤታዊ ያልሆኑ የሚወሰኑ የደንብ መተላለፍ ቅጣቶችን የማስፈፀም ጉዳዮች::

**፴፬. <u>የዳኝነት ሥልጣን ግጭት እና ሠበር</u>**

፩/ በድሬዳዋ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣንና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን መካከል የስልጣን ግጭት ሲያጋጥም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ያገኛል፣

፪/ የድሬዳዋ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ወደዚሁ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ጉዳዩን ሊያቀርብ ይችላል፣

፫/ በድሬዳዋ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በሰበር በታየ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለው የሚል ወገን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት የሰበር አቤቱታ ማቅረብ ይችላል::

(c) suits arising out of fiscal matters set out under Article 52 of this Charter;

(d) casea arising from the admini- strative contracts concluded by and among the executive bodies of the city Government or by and among the institutions under the ownership of the City Government;

(e) disputes arising between the executive bodies of the City Government and between the institutions under the City Government;

(f) cases arising in connection with the government houses administered by the City Government;

(g) applications to change names;

(h) applications of succession, Guardian ship /Tutor ship, or spousal partnership certificates; and

(i) applications for the declaration of absence and death.

2/ Criminal and Petty Offence Jurisdiction

(a) offences committed upon fiscal matters set out under Article 52 of this Charter;

(b) cases arising out of traffic and other petty offences;

(c) remand in custody and bail applications but without prejudice to the jurisdiction of Federal courts on federal offences;

(d) cases of execution of penalties imposed upon petty offences by the executive bodies of the City Government, provided that the other provisions of this Charter remain effective.

**34. Conflict of Jurisdiction and Power of Cassation**

1/ The Federal Supreme Court shall decide on conflict of jurisdiction that arises between the Diredawa city courts and Federal Court.

2/ A party alleging a fundamental error of law in a final judgment of the Diredawa City Appeallate Court rendered on an appeal case may institute before this Court a case which is the subject matter of power of Cassation.

3/ A party alleging a fundamental error of law in the ultimate judgment of The Diredawa City Appeallate Court subject to the power of cassation may institute before the Federal Supreme Court an application for the power of cassation.

**፴፭. የድሬዳዋ ከተማ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና አሠራር**

፩/ የከተማው ፍርድ ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይኖራቸዋል፡፡

፪/ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በከተማው ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር በሚወድቁ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፣

፫/ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች እና የመዳኘት ሥልጣን በተሰጣቸው ሌሎች አካላት የተወሰኑ ጉዳዮችን በይግባኝ ያያል፣

፬/ ስለሰበር አቤቱታ በዚህ ቻርተር አንቀጽ ፴፬ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል፣

፭/ የከተማው ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት የከተማው ምክር ቤት በሚያወጣው ሕግ ይወሰናል፡፡

**፴፮. የድሬዳዋ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ**

፩/ የከተማ ፍርድቤቶችን የዳኝነት ሥራ አካሄድ የሚመራ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በከተማው ምክር ቤት ይቋቋማል፣ ዝርዝሩ በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል፣

፪/ በጉባኤው ውስጥ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተወካይ ይኖራል፡፡

**፴፯. የዳኞች ሹመትና የሥራ ዘመን**

፩/ የከተማው የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በድሬዳዋ ከተማ ፍርድ ቤቶች የሚሾሙ ዕጩ ዳኞች ዝርዝር ለከተማው ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በእጩዎች ላይ ያለውን አስተያየት መጠየቅና ይህንኑ አስተያየት ከራሱ አስተያየት ጋር በማያያዝ በከንቲባው አማካኝነት ለከተማው ምክር ቤት የማቅረብ ሀላፊነት አለበት፣የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አስተያየቱን በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የእጩዎች ዝርዝር ለሹመት ለከተማው ምክር ቤት ይቀርባል፣

፪/ ዳኞች ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር ከፈቃዳቸው ውጭ ከዳኝነት ሥራ አይነሱም፡-

ሀ/ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ዳኛው የዲሲፒሊን ደንቦችን በመጣሱ ወይም የሙያ ብቃትና ጥራት በማጓደሉ ምክንያት ከሥራ እንዲሰናበት ሲወስን፣ ወይም

**35. Organization and Procedures of the Diredawa City Court**

1/ The City Court shall have first Instance Courts and Appeallate Court.

2/ A First Instance Court shall have first instance jurisdiction over matters falling under the jurisdiction of the City Court .

3/ The Appeallate Court shall entertain appeals over the decisions of First Instance Courts and other bodies entrusted with judicial powers.

4/ with out prejudice to the provisions of cassation under Article 34 of this Charter, Decisions rendered by the Appeallate Court shall be final.

5/ The organization of the Courts shall be detrmined by law the City Council makes.

**36. The Judicial Administration Commission of the Diredawa City Court**

1/ The Judicial Administration Comm- ission which directs the judicial operations of the City Courts shall be constituted; and the details thereof shall be set out by law the City Council makes.

2/ The Commission shall contain a representative of the Federal Courts.

**37. Appointments and Term of Office of Judges**

1/ The city Judicial Administration Commission has the responsibility to primarily shortlist judges for appointment and solicitthe the views of the Federal Judicial Administration Commission respecting the candidates and then to forward such views to the City Council through the Mayor, together with its recommendations. If the Federal Judicial Administration Commission does not submit its views within three months, the shortlist of the candidates shall be forwarded to the city Council for appointment.

2/ No judge shall not be removed from his office except for termination by resignation or for the following conditions:

(a) Where the Judicial Administration Commission decides to remove him for violation of disciplinary rules or on grounds of professional incompetence and poor performance; or

ለ/ በሕመም ምክንያት ዳኛው ሥራውን መቀጠል እንደማይችል ሲወሰን፣ እና

ሐ/ የከተማው ምክር ቤት ከግማሽ በላይ በሆነ ድምፅ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔውን ውሣኔ ሲያፀድቀው፣

## ፴፰. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ

የከተማው አስተዳደር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የዳኝነት ሥልጣን፣ አደረጃጀትና አሠራር በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ በተደነገገው መሠረት ይሆናል::

## ፴፱. የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት

፩/ የከተማው አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የሚቀርቡለትን የአስተዳደሩን ሠራተኞች ጉዳይ በይግባኝ የማየት ሥልጣን አለው::

፪/ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ አደረጃጀትና አሠራር በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል::

## ፵. የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ እና የከተማ ቦታ ማስለቀቅ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ

፩/ ጉባኤው በከተማው አስተዳደር የሚሰበሰቡ ግብሮችና ቀረጦችን በተመለከተ የሚቀርብለትን ይግባኝ የማየት እና የከተማን ቦታ ስለመያዝ እንደገና ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፪/፲፱፻፺፬ መሠረት ይሠራል፣

፪/ የጉባዔው አደረጃጀትና አሠራር በሌሎች አግባብ ያላቸው ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል::

## ፵፩. የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች

፩/ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ግምታቸው ከብር ፪ ሺህ /ሁለት ሺህ/ ያልበለጡ የንብረትና የገንዘብ ክርክሮችን የማየት ሥልጣን ይኖራቸዋል:: ይህ የፍትሐብሄር ሥልጣናቸው የሚተላለፉ የገንዘብ ሠነዶች ላይ ተመስርቶ የሚቀርቡ ጉዳዮችና የኢንሹራንስ ጉዳይ አይመለከትም፣

፪/ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የከተማውን የሃይጂንና የጤና አጠባበቅ ደንብ እና ሌሎችም ተመሳሳይ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ለማየት የሚኖራቸው ሥልጣን በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል፣

(b) Where it decides that a judge can no longer carry out his responsibilities on account of illness; and

(c) Where the City council approves by a majority vote the decision of the Judicial Administration Commission.

## 38. Labour Relations Board

The provisions of the labour Proclamation shall apply with respect to the jurisdiction, organization and procedures of the Labour Relations Board of the City Government.

## 39. The Civil Service Court

1/ The Civil Service Court of the City Government has the power to entertain appeal cases of The Civil Servants of the City Government lodged before it in accordance with the Civil Service law of the City Government.

2/ The Organization and procedures of the Civil Service Court shall be defined by the Regulations the City Council issues.

## 40. The Tax and Urban Land Clearance appeals Commission

1/ The Tax and Urban Land Clearance appeals Commission of the city shall have the power to entertain appeals lodged before it concerning taxes and duties collectable by the City Government and justiciabe issues under leas-hold laws.

2/ Without prejudice to the provisions of tax and leas-hols laws, the organization and the procedures of the Commission shall be defined by law the City Council makes.

## 41. Qebele Social Courts

1/ Qebele Social Courts shall have jurisdiction over cases regarding property and money claims where the amount involved does not exceed Birr 2000 (two thousand). There civil jurisdiction may not, however, include negotiable instruments and insurance claims.

2/ The jurisdiction of Qebele Social Courts over the city hygiene and public health contraventions and other similar petty offences shall be determined by law the City Council makes.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፬/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች በሚሰጧቸው ውሳኔዎች ቅሬታ ያለው ወገን ለከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፣ በዚህ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሣኔም የመጨረሻ ይሆናል፣

፬/ የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸው ጉዳዮች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ካለባቸው ለከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሰበር ሊቀርቡ ይችላሉ፣

፭/ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና አሠራር በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል::

## ክፍል ስምንት
## ስለ በጀት እና ፋይናንስ

### ፵፪. የበጀት ዓመት

የከተማው አስተዳደር የበጀት ዓመት የፌዴራሉ መንግሥት የበጀት ዓመት ይሆናል::

### ፵፫. የፋይናንስ ሥልጣን

የከተማው አስተዳደር አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚከተለው የፋይናንስ ሥልጣን ይኖረዋል፣

፩/ የፌዴራል መንግሥትንና የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶች እንዲሁም የኦሮሚያና የሱማሌ ክልል ተቀጣሪዎችን ሳይጨምር በከተማው ክልል ውስጥ በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ የሥራ ግብር በሕግ መሠረት ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

፪/ በከተማው ውስጥ የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

፫/ በከተማው ውስጥ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

፬/ በከተማው ከሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎች እና በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ሥር በሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የኤክሳይዝና የተርንኦቨር ታክስ ግብር ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

፭/ በከተማው ከሚኖሩ ግለሰብ ነጋዴዎች እና በከተማው ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ በፌዴራል መንግሥት ተሰብስቦ ለከተማው አስተዳደር ይሰጣል፣

፮/ በከተማው ውስጥ የከተማ ቦታ ኪራይና የቤት ግብር ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

3/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (4) of this Article, a party having dissatisfaction with a decision of a Qebele social court may appeal to the respective First Instance Court of the City. The decision rendered by the latter shall be final.

4/ Where a matter decided by a First Instance Court on appeal contains fundamental error of law, it may prove to constitute ground to lodge pleas of power of cassation before the Appeallate Court of the City.

5/ The organization and procedures of Qebele Social Courts shall be defined by law the City Council makes.

## PART EIGHT
## BUDGET AND FINANC

### 42. Fiscal Year

The fiscal year of the City Administration shall be that of the Federal Government.

### 43. Fiscal Powers

The City Administration shall have the following Fiscal Powers, and it shall

1/ assess and collect, according to law, income taxes from incomes earned in employment within the bounds of the City but with the exception of the employees of the Oromia Region, the Federal Government organs, including federal public enterprises.

2/ set and collect land use fees.

3/ levy taxes on incomes from agricultural activities in the City.

4/ assess and collect, according to law, from individual tradesmen located in the City profit taxes, excise taxes, and turn over taxes.

5/ receive value added taxes which shall be collected, according to law, by the Federal Government from individual tradesmen and public enterprises residing in the City.

6/ set and collect rens/lease prices of land in the City. It shall also levy housing taxes in the city.

፯/ በከተማው ውስጥ ከተከራዩ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ የገቢ ግብር ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

፰/ በከተማው ውስጥ ከሚፈፀሙ ውሎችና ስምምነቶች እንዲሁም ከንብረት ባለቤትነት ስም ምዝገባ ላይ የቴምብር ቀረጥ ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

፱/ የከተማውን መንገዶች የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች የመንገድ መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

፲/ በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ሥር በሚገኙ የመንግሥት ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

፲፩/ በከተማው ውስጥ በሚካሄዱ አነስተኛ የማዕድን ሥራዎች ላይ የማዕድን ገቢ ግብር፣ የሮያሊቲና የመሬት ኪራይ ክፍያዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

፲፪/ በከተማው ውስጥ የደን መጠቀሚያ ሮያሊቲ ክፍያ ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

፲፫/ በከተማው አስተዳደር ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

፲፬/ የከተማ ነክ ታክሶች እና ቀረጦች ይጥላል፣ የአገልግሎት ክፍያዎችን ይወስናል፣ይሰበስባል፣

፲፭/ በከተማው ውስጥ የፈጠራ መብትን በማከራየት በሚገኝ ጥቅም ላይ የገቢ ግብር ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

፲፮/ በከተማው ውስጥ በሚገኝ ንብረት የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ላይ ግብር ይወስናል፣ ይሰበስባል::

**፵፬. ገቢ ማስገኛ**

የከተማው አስተዳደር

፩/ በሕግ እስካልተከለከለ ድረስ የከተማው አስተዳደር ከሚያንቀሳቅሳቸው ተቋማት ወይም ከልዩ ፈቃድ የገቢ ማግኛ ተግባራት፣ ከጋራ ኢንቨስትመንት፣ ከፈንድ ኢንቨስትመንት፣ ከኪራይና ከለጋሾች ገንዘብ በማሰባሰብ ለከተማው ገቢ ያስገኛል፣

፪/ ክፍያ በሚያስገኙ ልዩ ልዩ ተግባራት ውል በመዋዋል መሳተፍ ይችላል::

7/ assess and collect, according to law, income taxes from houses and other properties let in the City.

8/ assess and collect stamp duties from contracts and agreements as well as from ownership title registration undertaken in the City.

9/ set road users charge and collect same from cars that use the roads of the City.

10/ set and collect rents from houses and other properties under the ownership of the City Administration.

11/ assess and collect, according to law, income taxes, royalties and land rents/lease prizes from mining operations undertaken in the City.

12/ set and collect, according to law, royalty for the use of forest resources in the city.

13/ set payments relating to the licenses and services delivered by the city Administration.

14/ levy municipal taxes and duties as well as set and collect service charges.

15/ assess and collect, according to law, income taxes from the gains of rentals of patent rights in the City.

16/ assess and collect, according to law, capital gins tax from a property situated in the city.

**44. Revenues Generation**

The City Administration shall

1/ generate revenues by means of the operations of the City or by undertaking through special permit income earning activities, such as joint investment, fund investment, rentals and fund-raising from donors, so long as such is not otherwise prohibited by law.

2/ participate through contractual comm- itments in a variety of remunerative activities.

## ፵፭. ብድር

፩/ የከተማው አስተዳደር የፌዴራል መንግሥት በሚፈቅደው መሠረት ከሀገር ውስጥ ምንጮች በአጭርና በረጅም ጊዜ ክፍያ ቀጥታ ብድር ወይም የዋስትና ሰነዶችን በመሸጥ ሊበደር ይችላል፣

፪/ ቀበሌዎች መበደር አይችሉም::

፫/ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በከተማው አስተዳደርና በቀሌዎች ተሳታፊነት የከተማው አሰስተደደር የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ፣ እንዲሁም የልማት ባንክ በሕግ መሠረት ሊያቋቁም ይችላል::

## ፵፮. ከፌዴራል መንግሥት ስለሚገኝ የፋይናንስ ድጋፍ

፩/ የከተማው አስተዳደር ሀላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት ይችል ዘንድ እንደአስፈላጊነቱ የአስቸኳይ ጊዜ፣ የማቋቋሚያና የልማት ዕርዳታ በፌዴራሉ መንግሥት ሊሰጠው ይችላል:: እንዲሁም ልማታዊ ጠቀሜታቸው ሀገር አቀፍ እንድምታ ላላቸው ፕሮግራሞች የሚያስፈልገውን ወጪ የፌዴራሉ መንግሥት ሊያግዘው ይችላል::

፪/ የፌዴራል መንግሥት ለከተማው አስተዳደር የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍና ብድር በተመለከተ የፌዴራሉ መንግሥት በቀጥታ ኦዲት ለማድረግና ገንዘቡ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለመቆጣጠር ሥልጣን ይኖረዋል::

## ፵፯. በጎ አድራጎት

የከተማው አስተዳደር ባለአደራና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ማቋቋም እና ሌሎች በሕግ መሠረት እንዲቋቋሙ መፍቀድ ይችላል::

## ፵፰. ያልተማከለ የፋይናንስ ሥርዓት

፩/ የቀበሌዎች የገቢ ክፍፍል ሥርዓት ተወዳዳሪነትንና ውጤታማነትን የሚያበረታታ እንዲሁም ፍትሐዊነ ትን መሠረት ባደረገ ቀመር እንዲከናወን ይደረጋል፣

፪/ ቀበሌዎች በከተማው ምክር ቤት ለተወሰነ ልዩ ሥራ የተመደበና የበጀት ድጎማ ይሰጣቸዋል:: ከድጎማ በጀቱ የተወሰነው በሥራቸው ለተዋቀሩት ማዘጋጃ ቤታዊ የሆኑና ያልሆኑ አገልግሎት አካላት ይከፋፈላል:: ክፍፍሉም የአገልግሎት አቅርቦትንና በልማት ወደ ኋላ የቀሩ ቀበሌዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል::

## 45. Borrowing

1/ The City Administration may, as per the authorization of the Federal Government, borrow directly from domestic and external sources by short-term and long-term repayment arrangement or by selling bonds.

2/ Qebele Administrations may not undertake borrowing.

3/ The City Administration may constitute, according to law, micro financing and Savings as well as Development Bank by forging partnership with governmental and non-governmental organizations as well as with Qebeles.

## 46. Financial Support from the Federal Government

1/ The City Administration may be granted by the Federal Government emergency, rehabilitation and development aid where necessary, with a view to enabling it to properly discharge its responsibilities. It may also be assisted by the Federal Government with respect to expenditures for programmes having countrywide developmental impact.

2/ The Federal Government shall have power to audit and make sure whether the loans and financial supports granted by it have been properly utilized by the City Administration.

## 47. Foundations

The City Administration may establish foundations and trusts as well as authorize others to establish such according to law.

## 48. Decentralized finance System

1/ It shall be ensured that the revenue sharing system of Qebeles be based on a formula which encourages competitiveness an effectiveness as well as that which takes into account equity.

2/ Qebeles shall be granted by the City Council center specific grant set aside for a specific purpose and block budget. A certain portion of such budget shall be disbursed for the Qebele municipal bodies. Such a sharing should take into account service delivery and the Qebeles lagging behind in their development.

፫/ የከተማው ምክር ቤት በልዩ ሁኔታ እንዲበረታቱ ለሚፈልጋቸው ፕሮጀክቶች ወጪ መሸፈኛ ለቀበሌዎች ከቀመር ውጪ ድጎማ ሊሰጥ ይችላል::

፬/ የከተማው የልማት ድርጅቶች ፣ መነሻ ካፒታል ይመደብላቸዋል::

፭/ ከከተማው ገቢዎች መካከል በቀበሌዎች ተሰብስበው ቀበሌዎች ራሳቸው ጥቅም ላይ የሚያውሏቸው ገቢዎች በከተማው ምክር ቤት ይወሰናሉ::

**፵፱. የፋይናንስ አስተዳደር**

፩/ የከተማው የፋይናንስ አስተዳደር ተቀባይነት ባላቸው የሂሣብ አያያዝ ሥርዓቶች፣ የሀገሪቱ የፋይናንስ ሕግና የከተማው ምክር ቤት ይህንኑ አስመልክቶ በሚያወጣው ሕግ መሠረት ይከናወናል፣

፪/ የከተማው አስተዳደር የከተማ ሀብት መጠበቁንና በሕግ መሠረት በሥራ ላይ መዋሉን የሚያረጋግጥ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ይኖረዋል፣

፫/ ከንቲባው ወቅታዊና ዓመታዊ የፋይናንስ ሪፖርት ለከተማው ምክር ቤት ያቀርባል:: የቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች በተመሳሳይ መልኩ ለቀበሌ ምክር ቤቶች ሪፖርት ያቀርባሉ፣

፬/ የከተማው አስተዳደር እና ቀበሌዎች የተሟሉ ኦርጅናል ገንዘብ ነክ ሰነዶች እንዲሁም ትክክለኛና የተሟላ የሂሣብ መዝገብ ይይዛሉ፣

፭/ ማንኛውም የተሰበሰበ ገንዘብ በፋይናንስ ሕግ በተፈቀደው መሠረት በባንክ ሂሣብ ውስጥ ይቀመጣል፣

፮/ የከተማው አስተዳደርና የቀበሌ አስተዳደሮች በስማቸው የሚከፈት የባንክ ሂሣብ ይኖራቸዋል፣

፯/ የከተማው አስተዳደር በሕግ መሠረት የግብር፣ የወለድና የመቀጫ ምሕረት የማድረግ እንዲሁም ዕዳን የመሠረዝ ሥልጣን ይኖረዋል::

**፶. የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር**

፩/ የከተማው የበጀት አስተዳደር የፌዴራሉን መንግሥት የበጀት መርህ የተከተለ ይሆናል፣

፪/ የከተማው በጀት በግልፅና ነዋሪውን በሚያሳትፍ መልኩ ይዘጋጃል:: የበጀት ጥያቄው ከመጽደቁ በፊት ባለ በጀት መሥሪያ ቤቶችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት አስተያየታቸውን ይሰጡበታል፣ የመገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም ነዋሪው እንዲሳተፍ ይደረጋል፣ በበጀት ላይ የሚደረጉ የምክር ቤቱ ስብሰባዎች ለነዋሪው ክፍት ይሆናሉ፣

3/ The City Council may grant subsidy to Qebeles to cover expenditures of projects that it desires to exceptionally encourage.

4/ Initial capital shall be set aside for the public enterprises of the City.

5/ Those revenues to be collected and utilized directly by Qebeles shall be specified by the City Council.

**49. Financial Administration**

1/ The financial Administration of the City shall be conducted according to accepted accounting norms, the country's finance law and the law the City Council makes.

2/ The City Administration shall have an internal control system which ensures the proper handling of the resources of the City and its utilization according to law.

3/ The Mayor shall submit to the City Council annual and periodical reports.

4/ The City Administration and the Qebeles shall maintain complete original financial documents as well as accurate and complete books of accounts.

5/ All collected funds shall only be deposited in bank accounts opened as per the authorization of finance laws.

6/ The City Administration and Qebeles shall have bank accounts to be opened in their names.

7/ The City Administration shall have power to lawfully revoke taxes, interests and fines as well as to write off debts.

**50. Budget Preparation and Administration**

1/ The city budget administration shall follow the budget principles of the Federal Government.

2/ The City budget shall be prepared transparently and in a manner that ensures the participation of residents. Budgetary offices and other concerned organs shall give their opinions on a budgetary proposal before it is approved. Mass media shall be employed to maximize the participation of residents. The meetings of the Council deliberating over budget proposal shall be open to residents.

፫/ የከተማው ምክር ቤት መጠባበቂያ በጀት ይመድባል፣ ከንቲባው መጠባበቂያ በጀቱን ለተፈላጊው ሥራ መድቦ በአግባቡ በሥራ ላይ ያውላል::

## ክፍል ዘጠኝ
## መስተጻድራዊ ግንኙነት

### ፶፩. የከተማው አስተዳደርና የፌዴራል መንግሥት ግንኙነት

፩/ የከተማው አስተዳደር የፌዴራሉ መንግሥት አካል ነው፣ ተጠሪነቱም ለፌዴራል መንግሥት ነው፣

፪/ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የፌዴራሉን መንግሥት በመወከል የከተማውን አስተዳደር ሥራ ይከታተላል፣ የከተማውን አቅም ግንባታ ሥራ ይደግፋል፣

፫/ የከተማው አስተዳደር ዕቅዱን፣ በጀቱንና የከተማውን አጠቃላይ ሁኔታ በተመለከተ ዓመታዊና ወቅታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ያቀርባል፣

፬/ በከተማው ውስጥ የሚገኙ የፌዴራል መንግሥት አካላት የከተማውን አዋጆችና ደንቦች የማክበር ግዴታ አለባቸው፣

፭/ ከተማውን የሚመለከቱ በፌዴራል ተቋማት የሚካሄዱ አገልግሎቶች ከከተማው አስተደደር ጋር በቅንጅትና በስምምነት ይፈፀማሉ::

### ፶፪. ከሌሎች ከተሞችና ክልሎች ጋር ስለሚኖር ግንኙነት

፩/ የከተማው አስተዳደር ከሀገሪቱ ክልሎችና ከተሞች እንዲሁም ከውጭ ሀገር ከተሞች ጋር ግንኙነት መፍጠር ይችላል፣

፪/ በሀገር ውስጥ የከተማው አስተዳደር ከልሎች ከተሞችና ክልሎች ጋር የነዋሪዎችን ጥቅም ለማስጠበቅ በፖሊሲዎች፣ በመሠረተ ልማትና በአገልግሎት አቅርቦት የልምድ ልውውጥ እና ትብብር ለማድረግ ይችላል፣

፫/ ከሀገር ውጭ እህት ከተሞች ጋር ግንኙነት ለመመሥረት ይችላል::

3/ The City Council shall allocate contingency budget. The Mayor shall allocate the contingency budget for the required work.

## PART NINE
## INTERGOVERNMENTAL RELATIONSHIPS

### 51. The City Administration and the Federal Government

1/ The City Administration shall be part of the Federal Government the City Administration shall be accountable to the Federal Government.

2/ The Ministry of Federal Affairs shall, as an agent of the Federal Government, follow up the performances of the City Administration and shall support the capacity-building undertakings of the City.

3/ The City Administration shall submit to the Ministry of Federal Affairs annual and periodical reports concerning its plans, budget and the overall status of the city.

4/ The organs of the Federal Government situated in the City have the duty to respect the Proclamations and Regulations of the City Administration.

5/ Services concerning the City and run by federal institutions shall be effected in partnership and agreement with the City Administration.

### 52. Relations with Other Cities and Regions

1/ The City Administration may establish relations with other cities and regions at home as well as with cities abroad.

2/ The City Administration may co-operate and exchange experiences with cities and regions at home in respect of policies, infrastructure and service delivery in order to promote the interests of residents.

3/ The City Administration may establish relations with sister cities abroad.

## ክፍል አስር
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፶፫. የከተማው የልማት ድርጅቶች

፩/ የከተማው የልማት ድርጅቶች በቦርድ ይመራሉ፣

፪/ የከተማው የልማት ድርጅቶች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የሚተዳደሩ ተቋማት ናቸው፣

፫/ ከንቲባው የቦርድ ሰብሳቢዎችንና አባላትን የከተማው ሥራ አስኪያጅ ከሚያቀርባቸው ዕጩዎች መካከል ይሰይማል፤ የቦርዱ ተጠሪነቱም ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፣

፬/ የልማት ድርጅቶች ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ሪፖርት ያቀርባሉ።

### ፶፬. ቻርተሩን ስለማሻሻል

የቻርተሩ ማሻሻያ ሃሣብ በከተማው ምክር ቤት ወይም አግባብ ባለው የፌዴራል መንግሥት አካል ሊቀርብ ይችላል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቻርተሩን የማሻሻያ ሃሣብ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ እንዲያገኝ ያስተላልፋል።

### ፶፭. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፪/ መሠረት የከተማው አስተዳደር እንደተቋቋመ ይህ ቻርተር ከመፅናቱ በፊት በየደረጃው ተቋቁመው የነበሩት የካውንስሉ አካላት ይበተናሉ፣

፪/ ይህ አዋጅ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ተኩል የሚቆይ ጊዜያዊ የከተማ አስተዳደር በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሰየማል፣ የከተማውን አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር ይረከባል። ጊዜያዊ አስተዳደሩ በዚህ ቻርተር ለከተማው ምክር ቤት እና ለከተማው ካቢኔ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል። የጊዜያዊ አስተዳደሩ ከንቲባ በዚህ ቻርተር ለከንቲባውና ለአፈጉባዔው የተሰጠ ሙሉ ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፣

## PART TEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 53. Public Enterprises of the City

1/ The public enterprises of the City shall be directed by a respective board.

2/ The public enterprises of the City are institutions which shall be governed as per the appropriate law.

3/ The Mayor shall designate board chairpersons and members from among candidates nominated by the City manager; and the accountability of boards shall be to the City manager.

4/ Public enterprises shall report to the City manager.

### 54. Amendment of the Charter

The Amendment proposal on this charter may be initiated by the City Council or by the appropriate organ of the Federal Government. The Prime Minister shall present the amendment proposals for the deliberation of the Council of Ministers and, upon approval, he shall ensure that it be decided upon by the House of Peoples Representatives.

### 55. Transitory Provisions

1/ The Diredawa Administration Council and Executive Committees that were functional at every level of the city before this Charter takes effect shall be dissolved at the instance of the constitution of the Diredawa City Provisional Administration in accordance with Sub-Article (2) of this Article.

2/ A provisional City Administration which shall remain in power up to one and half a year as of the effective date of this charter shall be designated by The Prime Minister. The Provisional Administration shall take over the powers and functions of the City Administration and shall have the powers and functions of the City Council and City Cabinet defined by this Charter. The Mayor of the Provisional Administration shall have the powers and functions given to the Mayor and the spokesperson of the City Council in this Charter.

፫/ ጊዜያዊ አስተዳደሩ፦

ሀ/ የቀበሌ ጊዜያዊ አስተዳደሮችን ይሰይማል፣

ለ/ የቀበሌ አከላለልን በዚህ ቻርተር መሠረት ተግባራዊ ያደርጋል፣

ሐ/ የከተማውን አስተዳደር የልማት ድርጅቶችን ጨምሮ ማዘጋጃቤታዊ የሆኑና ያልሆኑ አካላትን እንደገና ያደራጃል፣ ሠራተኞችንም በሚያፀድቀው መዋቅር መሠረት እንደገና ይመድባል፣ ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣

መ/ በሽግግሩ ወቅት በልማት፣ በዲሞክራሲ ግንባታና በአገልግሎት አቅርቦት የነዋሪውን የተደራጀ ተሳትፎ ለማጎልበትና የነዋሪውን ጥቅም የሚያስጠብቁ ውሳኔዎች ለመወሰን እንዲቻል ከነዋሪዎችና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተወከሉ ሰዎች የሚሳተፉበት አማካሪ ምክርቤቶች በከተማው ማዕከልና በቀበሌ ደረጃ ሊያቋቁም ይችላል፣ ዝርዝሩም በከተማው ጊዜያዊ አስተዳደር በሚወጣ ህግ ይወሰናል::

፬/ የከተማው ጊዜያዊ አስተዳደር ለሽግግሩ ወቅት፣

ሀ/ ለመልሶ ማደራጀት፣ ለሠራተኞች ኃላፊዎች መረጣና ድልድል የሚያገለግል የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ህግ ያወጣል፣ በመሆኑም የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ህጎች በሽግግሩ ወቅት በከተማው አስተዳደር ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፣

ለ/ የከተማውን አስተዳደር የልማት ድርጅቶች እንደገና በማደራጀት ሂደት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ዝርዝር ሁኔታ የሚወስን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ደንብ ያወጣል::

፭/ ጊዜያዊ አስተዳደሩ በሚያፀድቀው መዋቅር መሠረት የከተማው አስተዳደር አካላት ወይም ተቋማት በህግ መሠረት በሌላ አካላት ሲተኩ ወይም ሲዋሃዱ መብትና ግዴታቸው ለሚቋቋሙት አካላት ወይም ተቋማት ይተላለፋል፣ ወይም እንደየአግባቡ በጊዜያዊ አስተደደሩ ይወሰናል፣

፮/ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉና በዚህ ቻርተር መሠረት በከተማው የዳኝነት አካላት ሥልጣን ሥር የሚወድቁ ጉዳዮች በፌዴራል ፍርድ ቤት ውሣኔ ያገኛሉ:: ሆኖም አዳዲስ ጉዳዮች አግባብ ባላቸው የከተማው አስተዳደር የዳኝነት አካላት ይታያሉ::

3/ The provisional Administration

(a) shall designate Qebele provisional Administration

(b) shall implement Qebele delimit- ations in accordance with this Charter;

(c) shall reorganize municipal and non-municipal bodies, including public enterprise of the City; shall reassign, hire and dismiss their employees in accordance with the organizational structure it approves;

(d) may establish during the transition period City center and Qebele Advisory Councils in which residents and representatives of different parts of society shall participate to enhance the organized participation of residents in development, building of democracy, and service delivery as well as to render decisions which meet the interests of the public. the details thereof shall be set out by the Provisional Administration.

4/ The City provisional Administration shall

(a) Adopt civil Service Law applicable for the reorganization and selection of its staff both in recruitment and appointment positions. As a result, The federal Civil Servants laws shall not be applicable to the City Administration during the transition period.

(b) issue labour relations regulations, which set out the details under which the Labour Relations law becomes applicable in the process of reorganizing the public enterprises of the City.

5/ The rights and duties of the organs or institutions of the City Administration replaced or amalgamated as per the law and the organizational structure to be adopted by the Provisional Administration shall be transferred to the organs or institutions established, or it shall be decided by the Provisional Administration, as the case may be.

6/ Cases pending in the Federal Courts and falling under the jurisdiction of the City Courts in accordance with this charter shall continue to be entertained by the Federal Courts. Whereas, new cases shall be brought before the appropriate judicial organs of the City Adminis- tration.

**፶፮. ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ህጎች**

ከዚህ ቻርተር ጋር የሚቃረን ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ቻርተር በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

**፶፯. ቻርተሩ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ቻርተር በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ ሐምሌ 23 ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

**56. Inapplicable Laws**

Any law or practice in conflict with matters covered by this charter may not be applicable.

**57. Effective Date**

This Charter shall come into force as of the date of its publication on the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 30th day of July, 2004**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት